ይህ ስም ክቡር ነው።

ኢትዮጵያ የሚለው ስም ተራ ስም አይደለም። ብዙ ሚሊዮኖች እንዲሠው ያደረገ ስም ነው። አያሌዎች በስፖርት አደባባይ ካገኙት ድል በላይ ይህ ስም ሲጠራ አንብተዋል። ይህ ስም በቅዱስ መጽሐፍ ከአርባ አራት ጊዜ በላይ የተጠቀሰ ነው። ይህ ስም ሲጠራ ብዙዎች ኢትዮጵያውያን ደማቸው ይሞቃል፣ ስሜታቸው ይንራል፣ ነርቫቸውነም ይነዝራቸዋል።

ይህ ስም ከረሃብ እና ከእርዛት፣ ከድህነት እና ከችግር ጋር ሲነሣ የማያመው ዜጋ የለም። በዚህ ስም ሲለመንበት የማይቆስል ዜጋ የለም። በአንፃሩ ይህ ስም በክብር ሲነሣ ልቡ የማይሞቅ ሞራሉም የማይ ነሣሣ ዜጋ የለም። ተድባበ ጥላሁን ስለ ካዛንችስ የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት በጻፈው መጽሐፉ ላይ አንድ ግሩም እውነታ ይነግረናል። አብዛኛው ወደ ሴተኛ አዳሪዎቹ ቤት የሚመጣው ሰው የሚቀንሰው መቼ ነው? ለሚለው የነገረን ነገር።

ኢትዮጵያ በሩጫ ስታሸንፍ፣ ወይንም ብሔራዊ ቡድኑ ሲያሸንፍ፣ ያለበለዚያም ሀገሪቱ በአንዳች ነገር አሸነፈች ሲባል ብዙዎቹ የሴተኛ አዳሪዎች ደንበኞች ወደቤታቸው መሄድን ይመርጣሉ ይለናል። ለምን? እንደ እኔ ግምት አንዳች የሞራል ልዕልና፣ አንዳች የስብራት መጠገን፣ አንዳች የምግባር ከበሬታ ይሰማቸዋል ማለት ነው። ይህ ስም ከፍ ከፍ ሲል ብዙዎቹን ከድቀት እንደሚያነሣቸው ይነግረናል።

ይህ ሰም ክቡር ስም ነው።

ኢትዮጵያን የረሃብ ምሳሌ አድርጎ ካስቀመጠው መዝገበ ቃላት ይህንን ስም ለማስፋቅ በመላው ዓለም እንቅስቃሴ የጀመሩ ሀገር ወዳዶች አሉ። ይህ ስም ከዕድገት እና ከብልጽግና ጋር ብቻ፣ ከሰላም እና ከልዕልና ጋር ብቻ፣ ከሀብት እና ከፍቅር ጋር ብቻ እንዲነሣ በልማቱ ጎዳና ትግል የጀመሩ አሉ። ይህ ስም በመቻቻል እና በመፋቀር፣ ይቅር በመባባል እና በመግባባት ብቻ እንዲነሣ የሚደክሙ የሀገር ሽማ ግሌዎች አሉ። ይህ ስም ክቡር ስም ነውና።

ይህ ስም ፈጽሞ ከግብረ ሰዶማዊነት ጋር ለነሣ አይገባም። ፈጽሞ። 97 በመቶ ኢትዮጵያውያን ከሚጸየፉት ተግባር ጋር ሊነሣ አይገባም። ፈጽሞ። እነዚህ ሰዎች ስብሰባችንን በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ እያደረግን ነው አሉ። መገናኛ ብዙኃንም እያደረጉ ነው አሉላቸው። ይህ ለኛ ለኢትዮጵያውያን የአንገት መሰበር ነው። ለዚህ ስም ግብረ ሰዶም አይመጥነውም። ፈጽሞ።

ከአድዋ ድል ጋራ፣ ከአኩስም እና ከላሊበላ፣ ከሐረር አና ከጎንደር ሥልጣኔ ጋር የተጠራ ስም ከዚህ አስነዋሪ ተግባር ጋር ሊነሣ አይገባውም። ፈጽሞ። ከያሬድ እና ከአባ ጊዮርጊስ፣ ከቴዎድሮስ አና ከምኒሊክ፣ ከኃይሌ እና ከቀነኒሳ፣ ከደራርቱ እና ከመሠረት ጋር የተነሣ ስም ከግብረ ሰዶም ጋር ሊነሣ አይገባውም። ይህ ስም ክቡር ስም ነው።

ከማንኛውም ሥልጣኔ እና ዕድገት በፊት የመንፈስ ልዕልና ይቀድማል፡፡ በመንፈስ ያልበለጸገ ሕዝብ በቁሳዊ ነገር ሊበለጽግ አይችልም፡፡ ቢበለጽግም ዘላቂ አይሆንለትም፡፡

መንግሥት እንደ መንግሥት ይህንን ተግባር መከልከል ነበረበት፡፡ ይህ ስም ከግብረ ሰዶም ጋር አብሮ እንዳይነሣ መከልከል ነበረበት፡፡ እነዚህ ሰዎች ዛሬ በአዲስ አበባ መሰብሰብ ከጀመሩ፣ ነገ በአዲስ አበባ ይሰለፋሉ፣ ከነገ ወዲያ ደግሞ በአደባባይ ይፈጽሙታል፡፡

በአዲስ አበባ የልማት ጀግኖች ይሰብሰቡ፣ መሪዎች ይሰብሰቡ፣ አትሌቶች ይሰብሰቡ፣ አርቲስቶች ይሰብሰቡ፣ ደራስያን ይሰብሰቡ፣ የፖለቲካ መሪዎች ይሰብሰቡ፣ የባህል እና የእምነት መሪዎች ይሰብሰቡ፡፡ ባልገው ልጆቻችንን የሚያባልጉ፣ ያልበላንን የሚያክኩ፣ እየወጣነው ላለው ገደል ተጨማሪ ጉድጓድ የሚፈጥሩ ግብረ ሰዶማውያን እንዲሰበሰቡ መፍቀድ ግን በሕግ ወንጀል፣ በሃይማኖት ኃጢአት፣ በባህልም ነውር ነው፡፡

ይህ ስም ክቡር ስም ነው፡፡